

## ~ 7 ~

# “ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠንቀቁ”

### 7-1

ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን በአይሁድ መካከል ጎልተው የሚታዩ ስድስት ዓይነት እንቅስቃሴዎች (ፓርቲዎች) እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። እነርሱም፥

1ኛ. ፈሪሳውያን (ግብዞች)
2ኛ. ተቀናቃኞች
3ኛ. ዜለት (አፈግፋጊዎች)
4ኛ. ሰዱቃውያን (ቆሳቁሳውያን)
5ኛ. ሄሮዳውያን (ወላዋዮች)
6ኛ. ክርስቲያኖች (የክርስቶስ ተከታዮች)

ስለነዚህ እንቅስቃሴዎች መጠነኛ ሃሳብ ለማግኘት በቅደም ተከተል የምንማር ሲሆን፥ በመጀመሪያ የፈሪሳውያንን እንቅስቃሴ እንመልከት።

## የፈሪሳውያን እቅስቃሴ

ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን በአይሁድ መካከል ከነበሩት የኃይማኖት እንቅስቃሴዎች መካከል አንደኛው የፈሪሳውያን እንቅስቃሴ ነበር። ስማቸው ፓራሽ ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም “ከሌሎች የተለዩ” ማለት ነው። ይሄ ፈሪሳዊ በሚል የታወቀው ስም በብሉይ ኪዳን ዘመንም እንደተለዩ ክፍሎች ይታዩ እንደነበረ ግልጽ ነው። የነዚሁን ልዩ ልዩ የሆኑ የአይሁድ ክፍሎች እምነታቸውንና የሃይማኖት ልምምዳቸውን ጠንቅቆ ማወቅ የክርስትና እምነትንና ሕይወትን ለማወቅ ለምናደርገው ጥናት ጥሩ መግቢያ ይሆነናል። ፈሪሳውያን በእስራኤል ውስጥ ቋሚ የሃይ ማኖት ፓርቲ መሆናቸው የታወቀው ነርካነስ የተባለው ንጉሥ (135-104 ከክርስቶስ ልደት በፊት) በነገሠበት ዘመን ነበር። ታሪክ ጸሐፊው ዮሴፉስ እንደገለጸው ንጉሥ ነርካነስ የመጀመሪያው የፈሪ ሳውያን አባል ነበር። ይኸው ንጉሥ ሄርካነሳ ከሙሴ ሕግ ውጪ የሆኑትን ደንብና ሥርዓት እንዲ ጠብቁ ስለአስገደዳቸው ህዝቡ በእርሱና በፈሪሳውያን ላይ ትልቅ ጥላቻ አደረባቸው። እንዲሁም በመካከላቸውም በተፈጠረው አለመግባባት የተነሳ ብዙዎች ከሰዱቃውያን ጋር ተቀላቀሉ።

ፈሪሳውያን ንጹሕ ያልሆነውን ነገር የማይነኩ፣ አይሁድ ካልሆኑ ሰዎች ጋር የማይተባበሩ የተለዩ ሰዎች ነበሩ። ንጹሕ ካልሆነው ጋር ከሚተባበሩ ይልቅ ሞትን ይመርጡ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። ለምሳሌ በአንቲዮክስ ኤፒፋነስ ዘመን የግሪክን መንገድና አኗኗር የማይከተል ሁሉ በሞት የሚቀጣ መሆኑን ቢረዱም በግሪካውያን መንገድና ሥርዓት አንመራም በማለት እምነታቸው ይዘው የቆሙ ናቸው። ፈሪሳውያን የሚታወቁት በወግ አጥባቂነታቸው ብቻ አይደለም። የሙሴ ሕግ በመጽሐፍ

ተቀርጾ ከመቀመጡ በፊትም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕግ እንዲጠበቅና እንዳይጠፋ ያደርጉ ክፍሎች ናቸው። እንዲሁም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ተሰባብሮ የወደቀውን የአይሁድ እምነት (ሃይማኖት) ጠጋግነው ሕይ ወት እንዲዘራ ያደረጉት ፈሪሳውያን ናቸው። የእስራኤል ሕዝብ አንድነት የተመሠረተው በሙሴ ሕግ በቤተ መቅደሳቸውና በበጎ ምግባራቸው ላይ እንደሆነ ያምናሉ። የወደፊትም ተስፋቸው የተመሠረተው በፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ራሱ በልጆቹ በእስራኤላውያን ሕይወት እጁን የዘረጋ እንደሆነ ብቻ መሆኑና፥ ያም የሚሆነው እግዚአብሔር እራሱ በፈቀደው ጊዜ መሆኑን ፈሪሳውያን ጨም ረው ያምኑ ነበር። ፈሪሳውያን እምነታቸውና ሥርዓታቸው የሁሉም አንድ ዓይነት አይደለም። ሰባት የተ ለያዩ የፈሪሳውያን ዓይነቶች እንደነበሩ የአይሁድ ታሪክ ይመሰክራል። እነርሱም፥

1. **ጥቅም ፈላጊ ፈሪሳውያን**
   ሕግና ሥርዓት የሚጠብቁበት ዋናው ዓላማ፥ የግል ጥቅማቸውን በመፈለግ ወይንም ክብርንና ዝናን የሚያገኙበት ስለሚመስላቸው እምነቱን ይከተሉ ነበር።

2. **ጎባጣ ፈሪሳውያን**
   ከእውነት ያልመነጨ ትህትናቸውን ለሰዎች ለማሳየት ሲሉ አቀርቅረው የሚሄዱ ናቸው። በዚህ ምክንያት ከትከሻቸው የጎበጡ ናቸው።

3. **ደንቃፋ ፈሪሳውያን**
   ሴት በአጠገባቸው ስታልፍ ተሰዋስተው እንዳያዩ በማለት ዓይናቸውን ጨፍነው ስለሚሄዱ እንቅፋት እግሮቻቸውን እያቆሰለውና እየደሙ የሚኖሩ ወገኛ ፈሪሳውያን ናቸው።

4. **ጠምጣሚ ፈሪሳውያን**
   ንጹህ ያልሆነውን ነገር ዓይናቸው አይቶ እንዳይረክሱ ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ፊታቸውን በሻሽ ሸፍነው የሚሄዱ ናቸው።

5. **መሃይም ፈሪሳውያን**
   "ሕግን ጠብቁ" ብለው ይናገሩ እንጂ ራሳቸው የሚያስተምሩትን ሕግ ያወቁ አይደሉም። የሕግ አዋቂ የሆኑትን ሌሎች ፈሪሳውያንን በመጠየቅ አዋቂ መስለው እንዲያስተምሩ በግብዝነት መስለው የሚኖሩ አላዋቂዎች ነበሩ።

6. **ፈሪ ፈሪሳውያን**
   ሕግ አጥባቂነታቸው ከልባቸው አምነውበት ሳይሆን ወደፊት ፍርድ ይደርስብኛል በማለት ብቻ እምነቱን በፍርሃት የያዙ ናቸው።

7. **እውነተኛ ፈሪሳውያን**
   ከልባቸው እውነተኛ ፈሪሃ እግዚአብሔር [illegible] ደስ ለማሰኘት የሚሞክሩ ናቸው። በብሉይ ኪዳን በተለይም የዳዊት መዝሙር ስለ ፈሪሳውያን የከፋ አስተያየት አልነበረውም፤ ኢየሱስ በመቅደስ ውስጥ ይሰብኩት የነበረውን ይህን ያህልም አልተቃወማቸው። እንዲያውም "ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም" አለ። በተጨማሪ ግን "እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታደርጉ" በማለት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል (ማቴ. 23፥3)። ዮሐንስ መጥምቁ "የእባብ ልጆች" (ማቴ.3፥7) ሲላቸው ኢየሱስ ደግሞ "የተለሰኑ መቃብሮች" (ማቴ. 23፥27) ይላቸዋል። እውር መሪዎች ስለሆኑ ብዙዎችን ከእግዚአብሔር መንግሥት ያስወጡ ነበር (ማቴ. 15፥14፣ 23፥15)። ኢየሱስ ፈሪሳውያንን እየደጋገመ ለምን በኃይለኛ ቃል ይናገራቸው ነበር? ግብዞች ከዕውነተኛው ትምህርትና የዋህነት የራቁ፣ በሌሎች ላይ የሚፈርዱ፣ በልባቸው የተንኮል ሃሣብ የሞላባቸው ናቸው ይላቸዋል (ማቴ. 15፥7-8፣ 13፥5-23)። ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ያወገዘበት ዋናው ምክንያት ተናግረው የማያደርጉ ግብዞች በመሆናቸው

ነበር። ሸከም የሆነ ውጪያዊ ሥርዓትና ደንብ በመደንገግ የቅድስናን መንገድ ያቃለሉት በመሆናቸው ነበር። ኢየሱስ በመደጋገም ትምህርታቸውንና ልማዳቸውን እየጠቀሰ በግልጽ ስለነገራቸው ይሆናል በመስቀል መሞቱን ከደገፉት ክፍሎች መካከል ዋነኞች የሆኑት።

## "ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ"

የጥናታችን ዋና ዓላማው የፈሪሳውያንን የሕይወት ታሪክ ለማወቅ ብቻ አይደለም። የእነርሱ የግብዝነት መንፈስ በእኛም ዘመን ያለነውን ክርስትያኖችን ሕይወትም ነክቶ እንደሆነ ለመመርመርና ለመታረም ነው። ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ከአስጠነቀቃቸው ማስጠንቀቂያ አንደኛው "ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ" ሲል ነው። ለነዚያ በእርሱ እግር ሥር ለተማሩ ኩሩዎች "ከተራው ምዕመናን እንበልጣለን" ብለው ራሳቸውን ለሚገምቱ ደቀመዛሙርት ይሄ የክርስቶስ አባባል ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነገር ነበር። ቢሆንም "በአለባበ ሳችን፣ በመልካችን፣ በትምህርታችን፣ በዘራችን፣ ሌላው ቀርቶ በእምነታችንም ከሌሎች የተሻልን ነን" በማለት ራሳቸውን አሳድገው ሌሎችን አሳንሰው የሚያዩ ብዙዎች አይታጡም። ፈሪሳዊነት ወይንም ግብዝነት የትንሽነታችንን እውነተኛ አቋምና መልክ መሸፈኚያ ብልሀት ነው። በእውነት ትልቅ የሆኑ ዝቅ ማለት ወይንም ትሁት መሆን አይከብዳቸውም። እግዚአብሔር አብ ሁሉን ነገር እንደሰጠው ያወቀው ኢየሱስ ጎንበስ ብሎ፣ ፎጣ ይዞ፣ የራሱን ተማሪዎች እግር ለማጠብ መጎንበስ ያስቻለው ትልቁ ምስጢር እውነተኛ ትልቅነቱን ያረጋገጠ በመሆኑ ነው። ፈሪሳዊ ትልቅነቱን ለማሳየት የሚሞክረው ከውስጡ እውነተኛ የሆነ ትልቅነት ስለሌለው ብቻ ነው። ያለው ሰው እንዳለው ለማሳየት የመጨነቅ ባህሪ አይኖ ረውም። ፈሪሳዊ ከእውነት ለመሸሽ ይሞክራል። የሽሽቱም ባህሪ የሚታየው የራሱን ትልቅነት ለማሳየት በሚያደርገው ጥረት ነው። ኢየሱስ "ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ" ሲለን እውነት ያልሆነ ሕይወት እንዳንኖር ሲመክረን ነው። እንደፈሪሳውያን አምልኮታችን ከንቱ ድካም እንዳይሆን ይፈልጋል። "እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌሎች ሰዎች ደካማ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ" እያልን የራሳችንን ጽድቅ በመቁጠር ሌሎችን አሳንሰን እንዳናይ የክርስቶስን ትምህርት ምሳሌነትን መከተል እንዳለብን ያስጠነ ቅቀናል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**